## Views የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ

Political Views<<እኔ ሰላማዊ ነኝ>> መዝ.119(120)፥7 ስለ ምን እያሰብክ ነው ልትሉኝ ትችላላችሁ ስለ ሌላ ነገር ብጠየቅ በፍጥነት መልስ ለመስጠት እሞክር ነበር አሁን ግን የተጠየኩት ከመታወቅ በላይ የሆነውን የአምላኬን እና የጌታዬን ነገር በመሆኑ በጣም ማሰብ ነው ያለብኝ፥ በመሆኑም ስለሱ ለመናገር ባሰብኩ ቁጥር ሁሌም እንደማደርገው ሁሉ አሁንም በጣም ብዙ እጨነቃለው በደንብ አስባለው የምመርጣቸው ቃላቶች እንኳን የእርሱን ነገር ሊገልጡ እና ሊመሰክሩ ብቁ ስለማይሆኑ ገና አስባለው!!!!!!!!! አቤት ጌታዬ ይገርማል እኮ!!!!! እኔ በሕይወቴ አንድ ነገርን እመኛለው ጌታም እሷን እንዳይከለክለኝ ሌተ ቀን እለምነዋለው << አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ማዕባራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር በሙሉ ቀምሷል ደግሞም ያውቀዋል እና በቃና ሰርግ ላይ ሲጠራ የሰውን ሰርግ አደመቀ ያለቀውን ወይን በውሀ ለውጦ ታዳሚውን ሲያስደስት ሰርገኛውን ደግሞ ከእፍረት አዳነው ይህም ሆነው በእናቱ ምልጃ ነበር። ጌታ የሰውን ሰርግ እንዲህ አደመቀ የራሱ ሰርግ እንዴት ይሆን ይሆን ከዚህ ሰርግ ተገኝቼ ምናለ ስጋውን እና እውነተኛ የሆነውን ወይን ጠጥቼ ነፍሴን ባከበርኳት>>...

## Favorite Quotations

ሰለ አገሬና የሕዝቤ ልጆች ያለኝ ሙሾ

ውስጤ ይታወካል አንጀቴ ይላወሳል። ሁሉም ሕዝቧ እንደ ዓይን ብሌን የሚጠበቁ ቢሆኑም ፍቅር ግን የላቸውም። ፍቅር ለእነሱ የቋጥኝ ሸክም ነው። እርግጥ ፍቅርን ማውራት እንጂ መኖር አልቻሉትም፥ ያኛውን ትውልድን እንዳይመለከቱ ዓይናቸውን የጋረደውም የምዕራባውያን አርቴ ፊሻል ነገሮች ሁሉ እንደ ሱቅ በደረቴ ያሸበረቁ ናቸው። ነገን ከማሰብ ዛሬን መደሰት የሚል ፍልስፍና በመያዝ በፈጣሪ ስራ መታመን አይችሉም። ባሕር አቋርጠው ተሰደው እንኳን አመላቸው አይለቃቸውም።

ስለወገኔ ስደትና ስለወገኔ እንጀራ ፈላጊነት ሳስብ አምላኬን እንዲህ በማለት ተማጸንኩት <<አቤቱ እንደ ቀድሞ ዘመን ዘመናችንን አድስ>> አልኩኝ።

ይህ ሕዝብ በምን አንጀቱ ነው ይህን ቁጣ የሚሸከመው፥ በምን አቅሙ ነው ይህን ቀንበር የሚችለው። ያሳዝናል ሕጻናት ሮጠው መውደቅ አይችሉም አዛውንቱ እንደ በፊቱ ለወግ የሚሆን ርዕስ የላቸውም። ግን ለምን ይህ ሁሉ ነገር ከሌሎች ለይቶ በእኛ በረታብን። እውነት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አስታወሰኝ፥-<<እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ሁሉ ነገር ስለምን ደረሰብን>> ያሉ ሕዝቦች ትዝ አሉኝ። እርግጥ ነው ሊያስብል ይችላል። አሁን ያለው መከራ ምንጩ ታውቆ ምንጩን መድፈን ብንችል መለካም ነበር። ግን ምንጩን እንኳን ነው ማወቅ ያቃተን።

የሰውን ልጆች መላዕክት ቢያስተዳድሩን ኖሮ መንግስታዊ አዋጆች ባላ...ስፈለጉን ነበር። አንደ መላዕክት ብንሆን ደግሞ የውስጥም የውጭም ሕግ ባላስፈለገ ነበር። ግን ሰው በመሆናችን ሁሉም ነገር እኛን ለመቆጣጠር ያስፈልጋል። በተለይ በተለይ በስልጣኔ ጠኔ ውስጥ ያለው ትውልድ ልብ ሊለው የሚገባው ነገር ቢኖር ይህንን ነው። ግን ምን ያደርጋል በራሳችን ስህተተ የምንቀጣው ትውልድ በዛ። አዳም አጠፋ እኛ ሁላችንም ሞትን ለመሞት ተፈረደብን። ይሁን በፈጣሪ ቸርነት ደግሞ ሞትን ሁሉ ገደልነው በደሙም ተገዛን ነጻም ሆንን ከሞት እስራት ተፈታን።

ሕዝቤን የቸገርው እንጀራ ይመስል በየቀኑ ለእርቅ የሚሆን መደላያ የመደለያ ስንዴ ሲመጣ ችግራችንን የረሳን ይመስለናል። ግን አይደለም እውነት ማንም ያለተረዳው የሕዝቤ ችግር ቢኖር ፍቅር ነው። ለምን ይመስላችኋል ፍቅርን እንደ ስንዴ ሊረዱን ያልቻሉት ሐያላን አገራት። እኛን ያኖረን ፍቅርና እነርሱ የሚረዱን የፍቅር ስንዴ ሆዳችንን ሞልቶት በወረፋ እንኳን ሸማግሌውን ወጣቱ ይገፋዋል አሮጊቶችን የሚረዳ ጠፍቷል። ታዲያ ይህንን ሕዝቤን እንጀራ ነው ወይስ ፍቅር ነው የራበው?

የተሰደደውን ወገኔንስ እንጀራን ነው ወይስ ፍቅርን ነው የተራበው?። በስደት እንኳን ፍቅርን ገንዘብ ማድረግ ለምን አቃተው?። እባካችሁ ፍቅርን ልበሱት እርሱ ውበት ነው። የሀብትም ምንጭ ነው?።

እስቲ አብረን እንዲህ እንበል፥-

<< አቤቱ አንተ ሁሉን የምትችል አምላክ ሆይ እኛን ሕዝብህን ማረን የፍቅርህንም ዘይት አፍስስልን። ሕዝብህ ነንና አባት ሁነን፥ መልሰን እኛም እንመለስ ማረን እኛም እንፈወስ። በሰላምና በፍቅር እርስ በእርሳችን እንዋደድ ዘንድ መላው የሰውነት ክፍላችንን በፍቅር ምዕራፎች ገንባልን። ፍቅርን እንጂ ሀብትን አታላብሰን። እርሱ የሁሉ ፍጻሜ እርሱ ነውና>>

አሜን ኦ አሜን ለይኩን ለይኩን !!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!See More